ግንኙነት ወይም መዳራት፣ ስሜት የሚቀሰቀስበትን አካል መነካካት ወይም የሌላውን ሰው ዕርቃን መመልከት በዚህ ሐሳብ ውስጥ ይካተታሉ፤ ይህም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ግብረገባዊ መመሪያ መተላለፍ ነው (ዘሌ 18፥6-30፤ 20፥11-12:17:19-21፤ 1ቆሮ 6፥18፥ 1ተሰ 4፥3 ይመ)። (ለ) ሙሉ በሙሉ ስሜታዊ የሆነው ኢግብረገባዊ ወሲብ ወይም ቅንዝረኛነት (በግሪክ፣ ዩአሳለጂያጸ) በተለይም በወሲብ ረገድ ንጹሕ የሆነው ጠባይ የሚታይበትን ራስን መግዛት (1ጢሞ 2፥9 እና ጨዋነትን አስመልክቶ የቀረበውን ማብ ይመ) ቁም ነገር አድርጎ አለመቊጠርን ማለትም ግልጽ የሆነ ግብረገባዊ መርሕ አለመኖርን ያመለክታል። ይህም በኀጢአተኛ ወሲባዊ ስሜት ውስጥ መግባትን ወይም የፍትወት ስሜት መቀስቀስን የሚያካትት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በማይደግፈው ባሕርይ ውስጥ ገብቶ መጠመድ ነው (ገላ 5፥19፤ ኤፌ 4፥19፤ 1ጴጥ 4፥3፤ 2ጴጥ 2፥2:18)። (ሐ) አንድን ሰው መበዝበዝ ወይም አንድን ሰው ቁም ስቅሉን በማሳየት የራስን ጥቅም ማሳደድ ማለት (በግሪክ፣ "ፐሊዎኔክሴአ") የራስን ፍላጎት ለማርካት ሲባል እግዚአብሔር ለዚያ ሰው የፈቀደለትን ግብረገባዊ ንጽሕና እንዲያጣ ማድረግ ነው። በቅድስና መንገድ ተፈጻሚ መሆን የማይችለውን የሌላን ሰው ወሲባዊ ስሜት መቀስቀስ፣ ያንኑ ሰው መበዝበዝ ወይም እርሱን የራስ ስሜት መፈጸሚያ መሣሪያ ማድረግ ነው (1ተሰ 4፥6 ይመ፤ ከኤፌ 4፥19 ጋር ያነጻጽሩ)። (መ) ፍትወተ ሥጋ (በግሪክ፣ "ኤፒቱሚያ") ማለት አንድ ሰው ዕድሉ ቢጋጠመው የሚያረካውን ኢግብረገባዊ ስሜት ይዞ መገኘት ነው (ኤፌ 4፥19-22፤ 1ጴጥ 4፥3፤ 2ጴጥ 2፥18 ይመ፤ ማቴ 5፥28 እና ማብ ይመ)።

ግንኙነት በአጽንዖት ይገልጻል (በተለይ 2፥14-26)። (7) በኅብረተ ሰቡ መካከል ያለውን ኢፍትሐዊነትና አድላዊነት አጥብቆ በመቃወም ስለሚናገር አንዳንድ ጊዜ ያዕቆብ የአዲስ ኪዳኑ አሞጽ ተብሎ ይጠራል።

## የያዕቆብ መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የያዕቆብ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአራት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤

☐ 1 ☐ 2፥1—3፥13 ☐ 3፥14—4፥12 ☐ 4፥13—5፥20

### ማስታወሻ

